በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁጥር 206083

ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ሰለሞን አረዳ

ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- ወ/ሮ ፀሀይ ተፈራ   ከጠበቃ ግሩም አየለ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ ፡- 1ኛ. ወ/ሮ ወይንሸት ከበደ
2ኛ. አቶ ሚካኤል ገ/መስቀል } ጠበቃ ሙሉቀን ልመነህ

3ኛ. አቶ ቢኒያም ገ/መስቀል አልቀረቡም

4ኛ. ወ/ሮ እፀገነት ገ/መስቀል - ጠበቃ ሙሉቀን ልመነህ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ክርክሩ የቤት ሽያጭ ውልን መነሻ ያደረገ ሲሆን ጉዳዩ በተጀመረበት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽና የከሳሽ ተከሳሽ፤ 1ኛ፣ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች እንደየቅደም ተከተላቸው ተከሳሾች፣ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የተከሳሽ ከሳሽ እንዲሁም 4ኛ ተጠሪ ጣልቃ ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ሰኔ 1 ቀን 2010 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት ክስ የስር ተከሳሾች በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 4 ውስጥ የሚገኝ የቤት ቁጥሩ 154 የካርታ ቁጥሩ 20913 የሆነን ቤት ግንቦት 3 ቀን 1998 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ውል በብር 125,000 ሸጠውልኝ ብር 92,000 ተቀብለው ስመ ሀብቱን ለማዘወውር ተዋውለው ቤቱን ተረክቤያለው፡፡ ነገር ግን ስመ ሀብቱን ሊያዛውሩልኝ ፍቃደኛ ስላልሆኑ ቤቱ የእኔ መሆኑ ተረጋግጦ ስመ ሀብቱን እንዲያዛውሩልኝ እንዲሁም ወጪ እና ኪሳራ እንዲተኩልኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

3ኛ ተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው መልስ የማቅረብ መብታቸው የታለፈ ሲሆን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ ሰኔ 27 ቀን 2010 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርበው መቃወሚያው በብይን ታልፏል፡፡ በፍሬ ጉዳይ ላይ በሰጡት መልስ ውሉ ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት ያልተደረገ ስለሆነ ረቂቅ ነው፡፡ ቤቱ ቢገመት የሽያጭ ውሉ ሲደረግ ከነበረው ዋጋ በላይ ስለሚሆን በፍ/ሕ/ቁጥር 1710(2) መሰረት የ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ የሀሳብ ጉድለት ያለበት መሆኑን ያሳያል፡፡ የሽያጭ ውሉ በተደረገበት ጊዜ የቤቱ ስመ ሀብት በ1ኛ ተጠሪ ባለቤት እና በ2ኛ ተጠሪ አውራሽ አቶ ገብረመስቀል እንዳለ ስም ስለነበር ተጠሪዎች ቤቱን በራሳቸው መሸጥ በማይሉችሉበት ሁኔታ የተደረገ ውል ነው፡፡ እንዲሁም ቤቱ ሲሸጥ 2ኛ ተጠሪ 18 አመት ሳይሞላኝ እና 1ኛ ተጠሪ የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለመሸጥ የሚያስችል የሞግዚትነት ስልጣን ሳይኖራቸው የሽያጭ ውሉ የተደረገ በመሆኑ፤ በፍ/ሕ/ቁጥር 1013(3) መሰረት የውርስ ሀብትን ያለ ጋራ ስምምነት ማስተላለፍ ስለማይቻል እና ሌሎች የሚመለከታቸው ወራሾች ስላሉ ስመ ሀብቱ እንዲዞር የቀረበው ክስ ተገቢነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

4ኛ ተጠሪ ሰኔ 27 ቀን 2010 ዓ.ም ባቀረቡት የጣልቃ ገብነት አቤቱታ የሟች አቶ ገብረመስቀል እንዳለ ወራሽ መሆኔ ሐምሌ 25 ቀን 1992 ዓ.ም በፍርድ ተረጋግጧል፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት ሽያጭ እኔ ሳላውቅ እና ፍቃዴን ሳልሰጥ የተከናወነ እንዲሁም መሸጡን ላውቅ የምችልበት ሁኔታ ስላልነበረ ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንድገባ ይፈቀድልኝ በማለት ጠይቀው ተፈቅዶላቸው ቤቱ 1ኛ ተጠሪ እና ሟች ከመጋባታቸው ከ1971 ዓ.ም በፊት የተፈራ የሟች የግል ሀብት ስለሆነ እና በሽያጩም ስላልተስማማው የሟች ልጆች ከሆኑት የስር 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ጋር እኩል እንድንካፈል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

በሌላ በኩል 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ሰኔ 27 ቀን 2010 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ውሉ ሲደረግ 2ኛ ተጠሪ ለአካለ መጠን ያልደረሰ፤ የተጣለበትን የሕግ ክልከላ በመተላለፍ የሽያጭ ውሉ የተደረገ እና 1ኛ ተጠሪ ስለ 2ኛ ተጠሪ የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለመሸጥ ስልጣን ሳይኖራቸው እንዲሁም ሌሎች ወራሾች ሳይስማሙ የተፈፀመ የሽያጭ ውል ነው፡፡ ቤቱም ሊያወጣ ከሚችለው አምስት ሚሊዮን ብር በታች በብር 125,000 መሸጡ ለሕግ እና ሞራል ተቃራኒ ስለሆነ በፍ/ሕ/ቁጥር 1710(2) መሰረት የፈቃድ ጉድለት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አለበት፡፡ በመሆኑም  ግንቦት 3 ቀን 1998 ዓ.ም የተደረገው የሽያጭ ውል እንዲፈርስ እና አመልካች ቤቱን ለ12 ዓመታት ይዘው ሲገለገሉበት ስለቆዩ ያለፉት 2 ዓመታት የኪራይ ገንዘብ በወር ብር 10,000 ታስቦ በድምሩ ብር 120,000 እንዲከፍሉ ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች በጣልቃ ገብ አቤቱታ ላይ በሰጡት መልስ ጣልቃ ገብ የቤቱ መሸጥ ላይ በ1ኛ ተጠሪ በኩል ፍቃዳቸውን የገለፁልኝ ስለሆነ ፍርድ ቤት ቀርበው በቃለ መኃላ ያረጋግጡልኝ፤ ቤቱ በሀራጅ ከተሸጠ ዋጋው ዝቅተኛ ይሆናል በሚል ስጋት በጊዜው ያወጣል በተባለው ዋጋ ሸጠውልኛል፤ ድርሻቸውን ከመጠየቅ በዘለለ ሽያጩን ሊቃወሙ አይችሉም በማለት ተከራክረዋል፡፡ በተጨማሪም በቀረበባቸው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ላይ በሰጡት መልስም 2ኛ ተጠሪ ለአካለ መጠን ያልደረሰ ቢሆንም ሞግዚቱ 1ኛ ተጠሪ ንብረት ለመሸጥ ባላቸው ስልጣን አማካኝነት ውሉ ተፈርሞ ፀድቋል፡፡ የሀራጅ ሽያጩን አስቀርተው በድርድር መሸጣቸውም የንግድ ችሎታቸውን የሚሳይ እንጂ የገበያ ዋጋውን በማያውቁበት ሁኔታ የተደረገ ሽያጭ ነው አያስብልም፤ የፍ/ሕ/ቁጥር 1013(3) ም ለክርክሩ ተገቢነት የለውም፤ ውሉን ከተፈራረምን በኂላም የስር ተከሳሾች ወኪል ደረሰኝ እና የቤቱን ሰነዶች ሰጥተውኝ ቤቱን የተረከብኩ ስለሆነ ክሱ ተገቢነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ሰምቶ በአመልካች እና በስር ተከሳሾች መካከል ግንቦት 3 ቀን 1998 ዓ.ም ውል መደረጉ አልተካደም፡፡ የቀረበው ካርታ በስተጀርባው ወደ ተከሳሾች ዞሯል፤ በመሆኑም ውሉ በሕግ ተቀባይነት ያለው እንጂ ረቂቅ ነው ሊባል አይችልም፡፡ ቤቱም በሀራጅ ሊሸጥ ሲል በድርድር መሸጣቸው የተከሳሾችን የገበያ እውቀት ያላቸው መሆኑን የሚያሳይ እንጂ የገበያ ዋጋ አለማወቃቸውን አያሳይም ነገር ግን አመልካች ቤቱን የገዙት የቤቱ ስመ ሀብት በካርታው ጀርባ ላይ ለተጠሪዎች ሳይዞርላቸው እና በፍ/ሕ/ቁጥር 1195 መሰረት ካርታ ሳይሰራላቸው መሆኑን ከክርክሩ ተገንዝበናል፡፡ 4ኛ ተጠሪ ሽያጩ ላይ ፍቃዳቸውን ያልሰጡ ስለሆነና ወራሾች ተስማምተው የተፈጸመ ሽያጭ ስላልሆነ በፍ/ሕ/ቁጥር 1809(1)(2) መሰረት ውሉ ፈራሽ ነው፡፡ አመልካች ቤቱን በኪራይ ያልያዙ በመሆኑ የኪራይ ጥያቄው ተቀባይነት የለውም  በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ መወሰኑን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በበኩላቸው የሽያጭ ውሉ ሲፈርስ ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ አለመወሰኑን፤ የካሳ ጥያቄያቸው ውድቅ መደረጉንና ቤቱን እንዲረከቡ እንዲወሰንላቸው ያቀረቡት ዳኝነት መታለፉን በመቃወም ይግባኛቸው ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተለያየ መዝገብ አቅርበው መዝገቦቹ ተጣምረው ከተመረመሩ በኂላ ቤቱ የወራሾች የጋራ ንብረት መሆኑ አላከራከረም፤ ቤቱ ያልተከፋፈለ የውርስ ሀብት ስለሆነ ቤቱን በሽያጭ ወይም በማናቸውም መንገድ ለማስተላለፍ የሁሉም ወራሾች ፍቃድ ያስፈልጋል፡፡ ሽያጩን 1ኛ ተጠሪ እና ሞግዚት በሆኑላቸው 2ኛ ተጠሪ ስም ጭምር ያከናወኑ ከመሆኑ ውጪ ሌሎች ወራሾች ፍቃዳቸውን የሰጡ ስለመሆኑ በውሉ ላይ አልተመለከተም፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረትን በሞግዚት ለመሸጥ የፍርድ ቤትን ፍቃድ ሊኖር የሚገባ ስለመሆኑ በሰ/መ/ቁጥር 54827 ላይ የሕግ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡ አመልካች ቤቱን ሲገዙ የቤቱ ስመ ሀብት በሻጭ

ስም ያለ ስለመሆኑ ያላረጋገጡ እና ውሉን ለመዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት ስላላደረጉ የቅን ልቦና ገዢ ናቸው ሊባል አይችልም፡፡ ስለሆነም የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ መወሰኑ ተገቢ ነው፡፡ የሽያጭ ውሉ ለፈርስ ይገባል ከተባለ ስመ ሀብቱ ወደ አመልካች ሊዞር የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ ገዢ በስር ፍርድ ቤት በቤቱ ላይ የተለያዩ እድሳቶችን ስለማድረጋቸው ጠቅሰው የተከራከሩ ቢሆንም ግንባታው የቤቱን ይዘት የለወጠ ስለመሆኑ ገልጸው ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ የግንባታ ወጪው እንዲተካላቸውም የጠየቁት ዳኝነት ስለሌለ የግምባታ ወጪን ከውል መፍረስ ጋር ተያይዞ ለቀረበው መከራከሪያ ፍርድ ቤቱ ሊመረምር የሚገባ ሁኖ አልተገኘም፡፡ ነገር ግን ውሉ እንዲፈርስ ሲወሰን ተዋዋዮች ወደ ነበሩበት ሊመለሱ አይችልም በሚል ክርክር ባልቀረበበት የስር ፍርድ ቤት ተዋዋዮች ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ አለመወሰኑ ተገቢ አይደለም በሚል በዚህ ረገድ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ቤቱን የያዙት በሽያጭ ውሉ አማካኝነት ስለሆነ ውሉ እስኪፈርስ ድረስ ቤቱን ይዘው የመጠቀም መብት ስላላቸው ተጠሪዎች ቤቱ ላይ ያጡትን ጥቅም በካሳ መልክ እንዲወስንላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ውድቅ መደረጉ ተገቢ ነው፡፡ ተጠሪዎች በይግባኝ ክርክሩ የደረሰባቸውን የወጪ እና ኪሳራ ዝርዝር የማቅረብ መብት አላቸው በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ሚያዝያ 11 ቀን 2013 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታቸውን ያቀረቡት ይህን የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማሳረም ነው፡፡ የአቤቱታው ይዘት ባጭሩ አመልካች በተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ እንዲሁም በጣልቃ ገብነት አቤቱታው ግንቦት 3 ቀን 1998 ዓ.ም የተደረገው ውል እንዲፈርስ የቀረበው ዳኝነት በፍ/ሕ/ቁጥር 1808 መሰረት በ2 ዓመት ወይም አመልካች ቤቱን ከያዝኩት 15 ዓመት የሞላው ስለሆነ በፍ/ሕ/ቁጥር 1845 መሰረት በይርጋ ይታገዳል በማለት ክርክሬን አቅርቤያለው፡፡ 2ኛ ተጠሪ ውሉ በተደረገበት ጊዜ የ13 ዓመት ልጅ ሁኖ ክሱ በቀረበበት ጊዜ 25 ዓመት ስለሞላው በፍ/ሕ/ቁጥር 1810(1) መሰረት ለአካለ መጠን ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ በ2 ዓመት  ውስጥ ሊቃወም ይገባ ነበር፡፡ 4ኛ ተጠሪም የውል ይሰረዝልኝ ክሱን በፍ/ሕ/ቁጥር 1810 እና 1845 መሰረት በ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ ስላላቀረቡ በይርጋ ይታገዳል በማለት ያነሳውት መቃወሚያ መታለፉ አግባብ አይደለም፡፡ 4ኛ ተጠሪ በአካል ተገኝተው በውሉ ላይ ባይፈርሙም በሽያጭ ውሉ ላይ ለፈረሙት 3ኛ ተጠሪ በቁጥር 9894/1/96 መስከረም 5 ቀን 1996 ዓ.ም ውክልና የሰጡ ስለሆነ እንዲሁም 3ኛ ተጠሪ ከተሰጠው ውክልና ስልጣን ውጪ ሰርቷል ቢባል እንኳ አመልካች ቤቱን የገዛውት አባታቸው ባለባቸው እዳ ምክንያት ተፈርዶባቸው ቤቱ በሀራጅ እንዲሸጥ ማስታወቂያ ከወጣ በኂላ የተሻለ ዋጋ እንዲያወጣላቸው በድርድር ለመሸጥ ተስማምተው ስለሆነ እና 4ኛ ተጠሪ የቤቱን በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ልታስቀረው የምትችል ባለመሆኑ እኔ ሳላውቅ የተፈጸመ ሽያጭ ነው የሚለውን ክርክር የምታነሳበት ሁኔታ ስለሌለ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የፍ/ሕ/ቁ. 2207(1) (2) ድንጋጌን ይቃረናል፡፡ አመልካች ቤቱን ከገዛው በኂላ የነበረውን ቤት እና የቆርቆሮ አጥር ሙሉ ለሙሉ አፍርሼ 8 ክፍል ቤት እና የግንብ አጥር ስለሰራውበት ውሉ እንዲፈርስ ቢወሰን እንኳ ወደ ነበርንበት ልንመለስ ስለማንችል በፍ/ሕ/ቁጥር 1817 መሰረት የተዋዋዮች መብት እንዲስተካከል አለመደረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚል ነው፡፡

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

አቤቱታው በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ለክርክሩ መሰረት የሆነው ቤት የ1ኛ ተጠሪ ባለቤት እና ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተጠሪዎች አባት ሞት ምክንያት በነበራቸው እዳ ፍርድ ቤት በሐራጅ ሊሸጥ ሲል በወቅቱ የገበያ ዋጋ እንዲሸጥ ተስማምተው 4ኛ ተጠሪም ለ3ኛ ተጠሪ ውክልና ሰጥታ ሽያጩ ከተፈፀመ ከ10 ዓመት በላይ ቆይቶ የአሁኑ ክርክር በሻጮች እና ገዢ መካከል ሁኖ ባለበት ውሉ አልተመዘገበም ወራሾችም ፈቃድ አልሰጡም ተብሎ የተወሰነበትን አግባብ ከፍ/ሕ/ቁጥር 1808፣1810፤1845፣ 1815፣1817፣2207 እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 39336፣ 43226፣ 48094 ከሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም አንፃር ለማጣራት ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪዎች መልሳቸውን እንዲያቀርቡ ታዟል።

1ኛ፤ 2ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ጥቅምት 4 ቀን 2014 ዓ.ም የተፃፈ መልሳቸውን ያቀረቡ ሲሆን 3ኛ ተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ስላልቀረቡ መልስ የማቅረብ መብታቸው ታልፏል። የተጠሪዎች መልስ ይዘት ባጭሩ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ እና በ4ኛ ተጠሪ የጣልቃ ገብነት አቤቱታ ላይ ላይ አመልካች በሰጡት መልስ በፍ/ሕ/ቁጥር 1845 መሰረት ያቀረቡት 10 ዓመት ይርጋ መቃወሚያ የለም፤ 4ኛ ተጠሪም ለ3ኛ ተጠሪ ውክልና መስጠታቸውን እና በቤቱ ላይ የማሻሻያ ስራ ስለመስራታቸው መጠኑ ታውቅ እና ተገምቶ ያቀረቡት መከራከሪያ ስለሌለ በበዚህ ረገድ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ የቀረበው ቅሬታ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 329(1) መሰረት ተቀባይነት የለውም። ውሉ በተደረገበት ጊዜ የቤቱ ስመ ሀብት በአቶ ገብረመስቀል እንዳለ ስም ያለ፤ ከ1ኛ እስከ 4ኛ ባሉት ተጠሪዎች ስም ያልዞረና የባለቤትነት ሰነድ ያልተዘጋጀለት በስማችን ልንሸጠው የማንችል በመሆኑ እንዲሁም በውሉ ላይ በተጠቀሰው የወራሽነት ማስረጃም 4ኛ ተጠሪን በስም የሚጠቅስ ስለሆነ አመልካች 4ኛተጠሪ መብት እንዳለት ተገንዝበው ተገቢውን ማጣራት ሊያደርጉ ይገባ ነበር። ስሙ በወራሾች ነበር ቢባል እንኳ ቤቱን ለመሸጥ የሁሉም ወራሾች ስምምነት ያስፈልጋል። 4ኛተጠሪ በውሉ ላይ አልፈረሙም፤ ውሉ ስለመደረጉም የሚያውቁት ነገር አልነበረም፤ ውሉም በውል አዋዋይ ፊት ያልተደረገ ስለሆነ በፍ/ሕ/ቁጥር 1723 መሰረት ተቀባይት የለውም፤ የሽያጭ ውሉ ሰደረግም 2ኛ ተጠሪ ለአቅመ አዳም ያልደረሰ በመሆኑ በሞግዚትንት የተዋዋሉት 1ኛ ተጠሪ የፍርድ ቤትን ፍቃድ ሊያገኙ ይገባ ነበር፤ አመልካች 2ኛ ተጠሪን በሚመለከት የፍ/ሕ/ቁጥር 1810ን ጠቅሰው 2 ዓመት የይርጋ መቃወሚያ አንስተው የነበረ ቢሆንም የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ የባለቤትነት መፋለምን የሚመለከት በመሆኑ በይርጋ አይታገድም፤ በአመልካች ክስ መነሻነት ቀረበ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ስለሆነም ይርጋ መቃወሚያ ሊነሳበት አይገባም፤ ጉዳዩ ያስቀርባል ሲባል የተጠቀሱት ሰበር ውሳኔዎች ለጉዳዩ ተገቢነት የላቸውም፤ አመልካች በ4ኛ ተጠሪ ለ3ኛ ተጠሪ ተሰጥቷል የሚሉትን ውክልና በስር ፍርድ ቤት በማስረጃነት አልቆጠሩም፤ በውሉ ላይም 4ኛ ተጠሪ በውክልና አልተሰየሙም፤ አመልካች በቤቱ ላይ እድሳት ሰለማድረጋቸው ጠቅሰው የሚያቀርቡት መከራከሪያ በስር ፍርድ ቤት ግንባታው ስለመደረጉ እና ስለ ግንባታ ወጪው ያቀረቡት ማስረጃ ስለሌለ ወደ ነበርንበት እንዳንመለስ የሚያደርግ አንድም ነገር ስለሌለ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተገቢ ነው የሚል ነው።

አመልካች በበኩላቸው ጥቅምት 18 ቀን 2014 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልሳችውን ያቀረቡ ሲሆን የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል።

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የክርክሩ ሒደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ጭብጥ በስር ፍርድ ቤት ከተደረጉ ክርክሮች፣ በማስረጃ ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች እንዲሁም ለጉዳዩ ተገቢነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች በዋናነት የሚከራከሩት 2ኛ ተጠሪ ለአካለ መጠን ከደረሰ በ2 ዓመት ጊዜ ውስጥ ውሉ እንዲፈርስ ክስ ስላላቀረበ እና 4ኛ ተጠሪም ውሉ በተደረገ በ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ ውሉ እንዲፈርስ ስላልጠየቀ በይርጋ ይታገዳል በማለት ያቀረብኩት መቃወሚያ መታለፉ፤ ሽያጩ የተከናወነው 4ኛ ተጠሪ ለ3ኛ ተጠሪ በሰጡት ውክልና መሰረት ሁኖ እያለ ውሉን አልፈረሙም መባሉ፤ ውክልና አልሰጡም ቢባል እንኳ አመልካች ቤቱን በስምምነት ባልገዛው በሀራጅ የሚሸጥብትን ሁኔታ 4ኛ ተጠሪ ልታስቀረው ስለማትችል የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ መወሰኑ እንዲሁም የሽያጭ ውሉ ሊፈርስ ይገባል ቢባል እንኳ ቀድሞ የነበረውን ግንባታ አፍርሼ አዲስ ግንባታ ያካሔድኩ በመሆኑ በፍ/ሕ/ቁጥር 1817 የተዋዋዮች መብት እንዲጠበቅ በሚያስችል ሁኔታ አለመወሰኑ አግባብ አይደለም በማለት ነው፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው አመልካች በፍ/ሕ/ቁጥር 1845 መሰረት የ10 ዓመት ይርጋን፤ 4ኛ ተጠሪ ለ3ኛ ተጠሪ ውክልና መስጠታቸውን እንዲሁም ያደረጉት ማሻሻያ መጠኑን ጠቅሰው በስር ፍርድ ቤት ስላልተከራከሩ የቀረበው አዲስ ክርክር ተቀባይነት የለውም፤ ከ2ኛ ተጠሪ አንጻር ያቀረቡት የይርጋ መቃወሚያ ክርክሩ የመፋለም ስለሆነ በይርጋ አይታገድም፤ ሽያጩ የተደረገው የቤቱ ስመ ሀብት በተጠሪዎች ሳይዞር ስለሆነ፤ ንብረቱ የማይንቀሳቀስ ንብረት በመሆኑም በሞግዚቱ የተወከለው 1ኛ ተጠሪን በሚመለከት በፍርድ ቤት የተሰጠ ፍቃድ ስለሌለ፤ 4ኛ ተጠሪም በውሉ ላይ ስላልፈረሙ እና ውሉ በአዋዋይ ፊት ስላልተደረገ ውሉ ፈርሶ ወደ ነበርንበት እንድንመለስ መወሰኑ አግባብ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

የውርስ ሀብት ክፍፍል እስኪደረግ ድረስ በወራሾች መካከል ሳይነጣጠል የሚቆይ፤ ክፍፍሉ እስኪፈጸምም ወራሾች በውርስ ንብረቱ ላይ የሚኖራቸው መብት በፍትሐብሔር ሕጉ ስለ የጋራ ባለሀብትነት በተነገሩት ድንጋጌዎች የሚገዛ ስለመሆኑ በፍ/ሕ/ቁጥር 1060(1) እና (2) የተመላከተ ሲሆን ሞግዚት መሸጥ የሚችለው አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ንብረት የሆኑ የሚንቀሳቀሱ ግዙፍነት ያላቸው ንብረቶችን፤አክሲዮኖችንና የገንዘብ ሰነዶችን ብቻ ስለመሆኑ በተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀፅ 277(1) ላይ ተመላክቷል፡፡

በመጀመሪያ አመልካች በስር ፍርድ ቤት 2ኛ ተጠሪ ለአቅመ አዳም ከደረሰ በ2 ዓመት ጊዜ ውስጥ እንዲሁም 4ኛ ተጠሪ ውሉ በተደረገ በ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ የውል ይፍረስልኝ ክስ ስላላቀረቡ የተከሳሽ ከሳሽነት ክሳቸው እንዲሁም የጣልቃ ገብነት አቤቱታው በይርጋ ይታገዳል በማለት ያቀረብኩት መቃወሚያ መታለፉ አግባብ አይደለም በማለት የሚያነሱትን መከራከሪያ መመልከቱ አስፈላጊ ሁኖ አግኝተነዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ በተመለከተው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ግንቦት 3 ቀን 1998 ዓ.ም ተደረገ የተባለውን ውል መነሻ በማድረግ 1ኛ፣ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የቤቱን ስመ ሀብት እንዲያዞሩላቸው ለማስወሰን ክስ መስርተዋል፡፡ በዚህ መነሻነት 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ውሉ ሊፈርስ ይገባል የሚሉበትን

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ምክንያት ጠቅሰው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ያቀረቡ ሲሆን 4ኛ ተጠሪም በጣልቃ ገብነት አቤቱታቸው ውሉ እንዲፈርስ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች በ2ኛ ተጠሪ ላይ ያቀረቡትን የይርጋ መቃወሚያ ለማብራራት ውሉ በተደረገበት ጊዜ የ13 አመት ልጅ የነበረ እና ክሱ በተመሰረተበት ጊዜ እድሜው የ25 ዓመት ልጅ የነበረ መሆኑን ጠቅሰው የሚያቀርቡትን መከራከሪያ ተጠሪዎች አላስተባበሉም፡፡ ይህም 2ኛ ተጠሪ በሞግዚቱ አማካኝነት የተደረገውን የቤት ሽያጭ ውል የተቃወመው ለአቅመ አዳም ከደረሰ ከ2 ዓመት በኂላ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በፍ/ሕ/ቁጥር 1808(1) ከተዋዋዮቹ አንዱ ፍቃዱን በመሳሳት፣ በተፈፀመበት የተንኮል ወይም የማስገደድ ተግባር ወይም ችሎታ ሳይኖረው የሰጠ እንደሆነ ይህን ምክንያት በመጥቀስ እና በማስረጃ በማረጋገጥ ውሉ ፈራሽ እንዲደረግለት ዳኝነት የሚጠይቅበትን አግባብ የሚያመላክት ነው፡፡ በአንፃሩ በንዑስ አንቀፅ 2 ስር የተገለፀው የውል ጉዳዩ ህገ ወጥ ወይም ኢሞራላዊ የሆነ ወይም በሕጉ የተገለፀውን የአቀራረፅ ስርዓት ባለመከተሉ ከመጀመሪያውም ሕግ እውቅና የማይሰጠው እንዳልነበረ የሚቆጠር ቢሆንም ይመለከተኛል ባይ 3ኛ ወገን ወይም ተዋዋዮች ውሉ ዋጋ አልባ እንዲባል ዳኝነት የሚጠይቁበትን ሁኔታ የሚያመላክት ነው፡፡ ነገር ግን በዚህ አግባብ ውሉ ፈራሽ ወይም ዋጋ አልባ ነው በማለት እንዲወሰን ቀድሞ ዳኝነት ያልጠየቀበት ተዋዋይ በሌላኛው ተዋዋይ እንደ ውሉ እንዲፈፀምለት የጠየቀው እንደሆነ በፍ/ሕ/ቁጥር 1809 መሰረት ውሉ የማይረጋበትን ምክንያት በመጥቀስ በማንኛውም ጊዜ መቃወሚያ ሊያደረገው ይችላል፡፡ ይህ ድንጋጌ ዋጋ አልባ ወይም ፈራሽ ውሎችን በማለት ለይቶ መመዘኛ የማያስቀምጥ በመሆኑ ለሁለቱም ሁኔታዎች ተግባራዊ የሚሆን ድንጋጌ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ውሉ የማይረጋበትን ምክንያት በመጥቀስ መቃወሚያ አድረጎ ማንሳት የሚችለው በውሉ መሰረት መፈጸም ያልተጀመረ ከሆነ ብቻ ነው? ወይስ በሙሉ ወይም በከፊል ውሉ ከተፈጸመ ውሉ የማይረጋበትን ምክንያት መቃወሚያ አድረጎ ማንሳት ይችላል ወይስ አይችልም? የሚሉት ነጥቦች በትኩረት ሊመረመሩ ይገባል፡፡ በፍ/ህ/ቁጥር 1809 አገላለጽ ውሉ የማይረጋበት ምክንያት እያለ በውሉ መሰረት በሙሉ ወይም በከፊል ከተፈጸመ በተግባር ውሉ ተቀባይነት እንዳገኘ አመላካች ነው፡፡ አንድ ተዋዋይ በተግባር ተቀብሎ በውሉ መሰረት ተፈጽሞ እያለ ክስ ስለቀረበበት ብቻ ውሉ የማይረጋበትን ምክንያት በመጥቀስ የሚያቀርበው መቃወሚያ በተግባር የተቀበለውን የውል ውጤት የሚቃረን በመሆኑ መቃወሚያው ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም፡፡ ይህ ማለት ግን ውሉ አይረጋም የሚል ወገን ክስ አቅርቦ ውሉን ማስፈረስ አይችልም ማለት ባለመሆኑ በውሉ መሰረት በከፊል ወይም በሙሉ እንደውሉ ከተፈጸመ በህጉ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ክስ አቅርቦ ውሉን እስካላስፈረሰ ድረስ በውሉ መሰረት ሊፈጸም አይገባም በማለት የሚያነሳው መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም፡፡ በመሆኑም የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1809 ተፈጻሚ ሊሆን የሚችለው እንደውሉ ከመፈጸሙ በፊት ነው፡፡ በከፊል ወይም በሙሉ በውሉ መሰረት ከተፈጸመ በኂላ ውሉ የማይረጋበትን ምክንያት በመጥቀስ መቃወሚያ አድረጎ ማቅረብ ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ቀደም ሲል በሰበር መዝገብ ቁጥር2 12820 እና ሌሎች መዝገቦች የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ክስ ያቀረቡት በውል መሰረት እንዲፈጸም ወይም ቤቱ ለክርክሩ መሰረት የሆነው ቤት የእርሳቸው ነው ተብሎ ስመ ሀብቱ እንዲዛወርላቸው ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ከ1ኛ-3ኛ ባሉ ተጠሪዎች

*ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

በውሉ መሰረት የስመሀብት ዝውውር መፈጸም ያልጀመረ መሆኑን ያሳያል፡፡ ስለዚህ 2ኛ ተጠሪ በፍ/ሕ/ቁጥር 1809 መሰረት ውሉ የማይረጋበትን በፍ/ሕ/ቁጥር 1808 ላይ ከተጠቀሱት ምክንያቶች አንዱ የሆነውን ችሎታ ማጣት ውሉ እንዲፈጸም ክስ ሲቀርብባቸው በማኛውም ጊዜ ማንሳት የሚችሉ በመሆኑ አመልካች በ2ኛ ተጠሪ ላይ የፍ/ሕ/ቁጥር 1810(1)ን ጠቅሰው ያቀረቡት የ2 ዓመት የይርጋ መቃዊሚያ መታለፉ ተገቢ ነው፡፡ በሌላ በኩል አመልካች የ4ኛ ተጠሪ የጣልቃ ገብነት አቤቱታ በ10 ዓመት የሚታገድ መሆኑን ጠቅሰው በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት መከራከሪያ የለም፡፡ በጣልቃ ገብነት አቤቱታው ላይ በሰጡት መልስ የተከራከሩት ውሉ የተደረገው ከ15 ዓመት በፊት በነበረው የገበያ ዋጋ መሆኑን በመጥቀስ እንጂ ይርጋ መቃወሚያ በማንሳት አይደለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ያቀረቡት አዲስ ክርክር በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 329(1) መሰረት ተቀባይነት ያለው ሁኖ አላገኘነውም፡፡

በመቀጠል አመልካች ስመ ሀብቱ እንዲዞርላቸው ያቀረቡት ክስ ውድቅ ተደርጎ በአንፃሩ ውሉ እንዲፈርስ የመወሰኑ አግባብነት ተመለክተነዋል፡፡ ግንቦት 3 ቀን 1998 ዓ.ም የቤት ሽያጭ ውል መደረጉ፤ ውሉ በፍ/ሕ/ቁጥር 1723 መሰረት ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት አለመፈፀሙ፤ የሽያጭ ውል የተደረገበት ቤትም ከ2ኛ እስከ 4ኛ ስማቸው የተጠቀሰው ተጠሪዎች አባት በሆኑት ገብረመስቀል እንዳለ ስም ተመዘግቦ የሚገኝ በወራሾች መካከል ያልተከፋፈለ የውርስ ሀብት መሆኑ ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ የማይንቀሣቀስ ንብረትን የባለቤትነት መብት ለማስተላለፍ የሚደረግ ውል በሙሉ በፍርድ ቤት መዝገብ ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሠጠው አካል ፊት መደረግ ያለበት መሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1723(1) ላይ ተመላክቷል፡፡ ይህን የአፃፃፍ ሥርዓትን መከተል ውሉ በህግ ፊት የፀና እንዲሆን ከሚያስፈልጉ መመዘኛዎች አንዱ ነው፡፡ ነገር ግን ከ1ኛ-3ኛ ባሉት ተጠሪዎች ውሉ በሚመለከተው አካል ፊት ያልተደረገ ቢሆንም ውሉ የታመነ ስለሆነ ለውል ማፍረሻ ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡

በሌላ በኩል 2ኛ ተጠሪ ውሉ በተደረገበት ግንቦት 3 ቀን 1998 ዓ/ም ለአቅመ አዳም ያልደረሰ እና በ1ኛ ተጠሪ የሞግዚት አስተዳደር ስር የነበረ በመሆኑ በ1ኛ ተጠሪ ተወክሎ ውሉን 1ኛ ተጠሪ መፈረማቸው አላከራከረም፡፡ አመልካች ይህን ሲያከናውኑ ንብረቱ የማይንቀሳቀስ ንብረት እንደመሆኑ የፍርድ ቤት ፍቃድ ሊያገኙ ይገባ የነበረ ሲሆን አመልካች ማንኛውንም አይነት ውል 1ኛ ተጠሪ በሞግዚትነት ስልጣናቸው ሊፈጽሙ ይችላሉ ብለው ከሚከራከሩ በቀር በፍርድ ቤት ፍቃድ ያገኙ ስለመሆኑ ጠቅሰው የሚያቀርቡት መከራከሪያ የለም፡፡ ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ስር ፍርድ ቤቶችም በሕጉ አግባብ ፍርድ ቤት ፍቃድ ያልሰጣቸው መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ እንደዚሁም 2ኛ ተጠሪ ውሉ በተደረገበት ግንቦት 3 ቀን 1998 ዓ/ም ለአቅመ አዳም ያልደረሰ እና በ1ኛ ተጠሪ የሞግዚት አስተዳደር ስር የነበረ በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ በውሉ ላይ መፈረማቸው አላከራከረም፡፡ ሞግዚት መሸጥ የሚችለው አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ንብረት የሆኑ የሚንቀሳቀሱ ግዙፍነት ያላቸው ንብረቶችን፤ አክሲዮኖችንና የገንዘብ ሰነዶችን ስለመሆኑ በተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀፅ 277(1) ላይ ተመላክቷል፡፡ ይህ ድንጋጌ አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅን የማይንቀሳቀስ ንብረት ሞግዚቱ ከሚመለከተው አካል ተጨማሪ ፍቃድ እስካላገኘ ድረስ

በሽያጭ ለ3ኛ ወገን ማስተላለፍ የማይችል መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ በተቃራኒ 2ኛ ተጠሪ በማይንቀሳቀስ ውርስ ሀብቱ ላይ ያለውን መብት 1ኛ ተጠሪ በሽያጭ ለማስተላለፍ ያደረጉት ስምምነት የችሎታ(capacity) ጉድለት ያለበት መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

ከዚህም ሌላ የውርስ ሀብት በወራሾች መካከል ክፍፍል እስኪደረግበት ሳይነጣጠል የሚቆይና በዚህ ንብረት ላይ ወራሾች የሚኖራቸው መብትም በፍትሐ ብሔር ሕጉ ስለ የጋራ ባለሀብትነት መብቶች በተነገሩት ድንጋጌዎች የሚገዛ መሆኑ በፍ/ሕ/ቁጥር 1060(1) እና (2) ላይ ተመልክቷል፡፡ በዚህ አግባብ የጋራ ባለሀብትነትን የሚመለከተው የፍ/ሕ/ቁጥር 1266 የጋራ የሆነውን ንብረት ለመሸጥ፣ ለማስተላለፍ ወይም በዋስትና ለማስያዝ ወይም የተመደበበትን አገልግሎት ለመለወጥ የጋራ ባለንብረቶቹ የሁሉም ስምምነት የሚያስፈልግ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ 4ኛ ተጠሪ የሟች አቶ ገብረ መስቀል እንዳለ ወራሽ እና የውርስ ሀብቱ ተከፋይ መሆናቸውን አመልካች ክደው የሚያቀርቡት መከራከሪያ ካለመኖሩም በላይ ወራሽ መሆናቸውም በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች 4ኛ ተጠሪ ለወኪሏ 3ኛ ተጠሪ በሰጠችው ውክልና አማካኝነት ፈርማለች በማለት የሚከራከሩ ቢሆንም ይህን ክርክር በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር በመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 329(1) መሰረት ተቀባይነት የለውም፡፡ በተጨማሪም አመልካች በስር ፍርድ ቤት የተከራከሩት 4ኛ ተጠሪ ሽያጩን የማትቃወም መሆኑን በእናቷ አማካኝነት ገልጻልኛለች ይህንንም በፍርድ ቤት ቀርበው በቃለ መኃላ ያረጋግጡልኝ በሚል መሆኑን ከፍርዱ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህም 4ኛ ተጠሪ ከላይ በተገለፁት የፍትሐ ብሔር ሕጉ ድንጋጌዎች መሰረት ህጋዊ በሆነ መልኩ ተወክለው የውል ስምምነቱ ላይ እንዳልፈረሙ የሚያስገነዝብ ሲሆን ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የስር ፍርድ ቤቶችም 4ኛ ተጠሪ አለመፈረሟን አረጋግጠዋል፡፡ በመሆኑም በእነዚህ ዝርዝር ምክንያቶች አመልካች ስመ ሀብቱ እንዲዛወርላቸው ያቀረቡት ዳኝነት ውድቅ ተደርጎ ውሉ እንዲፈርስ የተሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሁኖ አላገኘነውም፡፡

በመጨረሻም አመልካች ውሉ እንዲፈርስ ቢወሰን እንኳ ወደ ነበርንበት መመለስ ስለማንችል የተዋዋዮች መብት ባስከበረ መልኩ ሊወሰን ይገባል በማለት የሚያነሱት መከራከሪያ የመረመርን ሲሆን አመልካች ለዚህ ክርክራቸው በምክንያትነት የሚጠቅሱት በይዞታው ላይ ቀድሞ የነበረውን የቆርቆሮ አጥር አፍርሼ 8 ክፍል ቤት በመገንባት የግንብ አጥር አሰርቻለው በሚል ነው፡፡ ውለታውን ለመፈጸም የተሰራውን ስራ ለማፍረስ የማይቻል ሲሆን ወይም አስቸጋሪ ሁኖ ሲገኝ ወይም ከፍ ያለ መሰናክል የሚያመጣ ሲሆን ተገቢ የሆነው ኪሳራ እንዲከፈል በማድረግ እነዚህ የተሰሩ ስራዎች እንደረጉ እንዲቀሩ የሚደረግ ስለመሆኑ በፍ/ሕ/ቁጥር 1817 ላይ ተመልክቷል፡፡ ነገር ግን አመልካች በስር ፍርድ ቤቶች በይዞታው ላይ ተጨማሪ ግንባታ ያከናወኑ መሆኑን ጠቅሰው የተከራከሩ ከመሆኑ ውጪ ግንባታው በቀድሞው ግንባታ ላይ መሰረታዊ ለውጥ ያደረገ መሆኑን፣ የወጪ መጠኑን እና ዝርዝሩን በመግለፅ ወደ ነበርንበት ልንመለስ አንችልም በማለት ያቀረቡት መከራከሪያ የለም፡፡ ውሉ እንዲፈርስ ሲደረግም ተዋዋዮች ቀድሞ ወደ ነበሩበት ቦታ እንዲመለሱ የሚደረግ መሆኑ በፍ/ሕ/ቁጥር 1815 ላይ በተገለፀው አግባብ ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ መወሰኑ ህጉን እና የግራ ቀኙን ክርክር ያገናዘበ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች በይዞታው ላይ ያደረጉትን ተጨማሪ ግንባታ ወጪ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በሚመለከት በግልጽ ክስ አቅርበው ዳኝነት ከሚጠይቁ በቀር በዚህ ረገድ ያቀረቡት ቅሬታ ተገቢነት ያለው አይደለም፡፡

ሲጠቃለል አመልካች ያልተከፋፈለ የጋራ የውርስ ሀብት በሆነ ቤት ላይ ከ1ኛ-3ኛ ተጠሪዎች ጋር ያደረጉት የሽያጭ ውል የ2ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች የችሎታ ጉድለት ያለበት በመሆኑ የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ ተወስኖ ግራ ቀኙ ወደነበሩበት እንዲመለሱ ማለትም አመልካች ለተጠሪዎች ቤቱን እንዲያስረክቡ ተጠሪዎች ደግሞ ከአመልካች የተቀበሉትን የሽያጭ ገንዘብ ብር 92,000(ዘጠና ሁለት ሺ) እንዲመለሱ በመወሰኑ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሌለ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 66070 ጥቅምት 21 ቀን 2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 247152 ጥር 18 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት አሻሽሎ የሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

አ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም